በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
FEDERAL ETHICS AND ANTI-CORRUPTION COMMISSION

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ቀን
Date 30-11-2017
ቁጥር
Ref. No. 20/00950/ፌሥ/81

ለክቡር የሙስና መከላከል ጥናትና ክትትል ዘርፍ ም/ኮሚሽነር ጽ/ቤት

ፌ.ሥ.ፀ.ሙ.ኮ

ጉዳዩ፡- የሙስና መከላከል ጥናት ጥራትና ተገቢነት ማረጋገጫ ፕሮቶኮል ቁጥር 002/2017 ሥራ ላይ እንዲውል ስለመላክ፣

የኮሚሽኑ ማኔጅመንት ኮሚቴ በቀን ሐምሌ 4 ቀን 2017 ዓ.ም በቃለ ጉባኤ ቁጥር 15 ባፀደቀው መሠረት የሙስና መከላከል ጥናት ጥራትና ተገቢነት ማረጋገጫ ፕሮቶኮል ቁጥር 002/2017 ሆኖ የተመዘገበ መሆኑን እየገለጽኩ፣ ፕሮቶኮሉ በውጤታማነት ሥራ ላይ እንዲውል ክትትል እንዲደረግ አሳስባለሁ።

ወጣቶችን ያማከለ የፀረ ሙስና ትግል፣

የነገን ስብዕና ይገነባል!

ሳሙኤል ኡርቃቶ ኩርኬ (ፒኤችዲ)
ኮሚሽነር

ግልባጭ

ለኮሚሽነር ጽ/ቤት

ፌ.ሥ.ፀ.ሙ.ኮ

የፌደራል ሥነ- ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን

የሙስና መከላከል ጥናት ጥራትና ተገቢነት ማረጋገጫ ፕሮቶኮል

ፕሮቶኮል ቁጥር 002/2017

ሐምሌ፤ 2017 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የፌደራል ስነ- ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን

# የሙስና መከላከል ጥናት ጥራትና ተገቢነት ማረጋገጫ ፕሮቶኮል

## ፕሮቶኮል ቁጥር 002/2017

ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመታገል ዋነኛ መሳሪያ ከሆኑት ስልቶች አንዱ በተቋማት የሚከናወን የሙስና መከላከል የአሰራር ሥርዓት ጥናት ስራ በመሆኑ፣

ኮሚሽኑ በመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ በመንግስት የልማት ድርጅቶች እና በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ ለሙስናና ብልሹ አሰራር የተጋለጡ እና ሊጋለጡ የሚችሉ የአሰራር ስርዓቶችን በማጥናት ወይም እንዲጠኑ በማድረግ የመፍትሔ/የማሻሻያ/ ኃሳብ እንደሚያቀርብ፣ ተግባራዊነቱን እንደሚከታተል እና በማይፈፀሙት ላይ ተገቢ የሆነ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ በህግ የመመርመርና የመክሰስ ስልጣን ላለዉ አካል የሚያቀርብ መሆኑን፣

የሙስና መከላከል ጥናት በመንግስት መ/ቤቶች፣ በመንግስት የልማት ድርጅቶች እና ሕዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ በማከናወን በተቋማቱ የግልፅነትና የተጠያቂነት አሰራር እንዲኖር የሚያስችል በመሆኑ፣

ኮሚሽኑ ቁልፍ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የሚያከናውናቸው የሙስና መከላከል ጥናቶች አስቀድሞ በተቀመጡ ጥራትና ተገቢነትን ሊያረጋግጡ በሚችሉ ስታንዳርዶች መምራትና ማከናወን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የፌደራል የሥነምግባርና የሥነምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ይህን የሙስና መከላከል ጥናት የጥራትና ተገቢነት ማረጋገጫ ፕሮቶኮል አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ ፕሮቶኮል “የፌደራል የሥነምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን የሙስና መከላከል ጥናት የጥራት ተገቢነት ማረጋገጫ ፕሮቶኮል ቁጥር 001/2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ፕሮቶኮል ውስጥ ፡-

1. "**ኮሚሽን**" ማለት የፌደራል የሥነምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ነው፤
2. "**አዋጅ**" ማለት የፌደራል የሥነምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ እንደገና ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 1236/2013 ነው፤
3. "**የኮሚሽኑ የበላይ አመራር**" ማለት የኮሚሽኑ ኮሚሽነር ወይም ምክትል ኮሚሽነር ማለት ነው፣
4. “**ተቋም**” ማለት የሙስና መከላከል ጥናት የሚከናወንበት የመንግስት መ/ቤት፣ የመንግስት የልማት ድርጅት እና ሕዝባዊ ድርጅት ነው፣
5. “**የመንግስት መስሪያ ቤት**” ማለት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በመንግስት በጀት የሚተዳደር እና የፌዴራል መንግስቱ ስራዎች የሚከናወኑበት ማናቸውም መስሪያ ቤት ነው፣
6. “**የመንግስት የልማት ድርጅት**” ማለት የመንግስት ባለቤትነት ድርሻ በሙሉ ወይም በከፊል ያለበት ማንኛውም የፌዴራል መንግስት የልማት ድርጅት ወይም የአክሲዮን ኩባንያ ነው፣
7. “**ህዝባዊ ድርጅት**” ማለት በማንኛውም አግባብ ከአባላት ወይም ከህዝብ የተሰበሰበ ወይም ለህዝባዊ አገልግሎት ታስቦ የተሰበሰበ ገንዘብ፣ ንብረት ወይም ሌላ ሃብትን የሚያስተዳደር አካልንና አግባብነት ያለው ኩባንያን የሚያካትት የግል ዘርፍ ነው፣
8. "**ፕሮቶኮል**" ማለት ኮሚሽኑ በመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ በመንግስት የልማት ድርጅቶች እና በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የሙስናን መከላከል ጥናቶችን ለማካሄድ የሚመራበት የአሠራር ሂደትን የሚያሳይ ሰነድ ነው፤



የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
The Federal Ethics and Anti-Corruption Commission

9. "**ሙስና**" ማለት የተሰጠ ኃላፊነትን ለግል ወይም ለቡድን ጥቅም ሲባል ስርዓትን፣ ህግን፣ ደንብን እና የአሰራር መርሆችን የመጣስ ተግባር ነው፡፡

10. "**የሙስና መከላከል ጥናት**" ማለት በተቋማት ውስጥ ለሙስናና ብልሹ አሰራር ተጋላጭ ወይም ሊጋለጡ የሚችሉ የአሰራር ስርዓቶችን በጥናት በመፈተሽ ግኝቶችን መሰረት በማድረግ ምክረ-ኃሳብ የሚቀርብበት የአሰራር ስልት ነው፤

11. "**ለሙስና የተጋለጠ አሰራር**" ማለት በአንድ የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራት በሕግ ከተቀመጠው አሰራር ወጣ ያሉና ሙስናና ብልሹ አሰራር እንዲከሰት በር የሚከፍት ወይም ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር አሠራር ነው፤

12. "**ብልሹ አሰራር**" ማለት በመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ በመንግስት የልማት ድርጅቶች እና ህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ ከህብረተሰቡ ጥቅም ይልቅ የራስን ጥቅም በማስቀደም ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ሲባል የአሰራር ሥርዓትን ወደ ጎን በማድረግ የሚከናወን የአሠራር ችግር ወይም ክፍተት ነው፣

13. "**ቁልፍ የሆኑ ጉዳዮች**" ማለት ኮሚሽኑ በተመረጡና ችግር ፈቺ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ጥናት የሚደረግባቸው ርዕስ ጉዳዮች ማለት ነው፣

14. "**የመረጃና ማስረጃ መሰብሰቢያ ስልቶች**" ማለት እየተጠና ካለው ጥናት ጋር በተያያዘ ለምን፣ እንዴት፣ መቼ፣ በማን፣ማን እና የት የሚሉትን ጥያቄዎች ሊመልስ የሚችል የመረጃ ማሰባሰቢያ ስልት ነው፣

15. "**ምክረ ኃሳብ**" ማለት በተካሄደ የሙስና መከላከል ጥናት ግኝትን መሰረት ያደረገና ችግሮቹን ለማሻሻል የሚያስችል የመፍትሔ ኃሳብ ነው፣

16. "**ድጋፍና ክትትል**" ማለት የተካሄደ የሙስና መከላከል ጥናቶችን መሠረት በማድረግ ተጠኚ ተቋማት በተሰጣቸው ምክረ ኃሳብ መሰረት ተግባራዊ ስለማድረጋቸው ድጋፍና ክትትል የሚደረግበት አሰራር ነው፤

17. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትም ፆታ ይጨምራል፡፡

## 3. የፕሮቶኮሉ ዓላማ

ፕሮቶኮሉ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1. ኮሚሽኑ የሙስና መከላከል ጥናቶች ጥራትና ተገቢነታቸው በተረጋገጠ፣ ወጪ ቆጣቢና በተቀመጠ የጊዜ ሰሌዳ እንዲከናወን ለማስቻል፤

2. በተጠኑ የሙስና መከላከል ጥናቶች ላይ ድጋፍና ክትትል በማድረግ የማሻሻያ ምክረ ኃሳቦች ተግባራዊ እንዲሆኑንና ሳይፈፀሙ ሲቀርም ተጠያቂነት እንዲረጋገጥ ለማድረግ ነው፡፡፡

4. **የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ ፕሮቶኮል በፌደራል የመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች እና ህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ በሚካሄዱ የሙስና መከላከል አሰራር ስርዓት ጥናቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የሙስና መከላከል ጥናት ፕሮጀክት የፕሮፖዛል ዝግጅት እና የጥናት ምዕራፍ ስራዎች

5. **የሙሰና መካላከል ጥናት ፕሮጀክት ዝግጅት ግምገማ እና የመረጣ መነሻዎች፤**
   1. ዘርፍ-ተኮር እና ችግር-ፈቺ የጥናት ርዕሰ-ጉዳይ መሆኑ፣
   2. ኮሚሽኑ በተለያዩ አማራጮች ስለዘርፉና በሥሩ ባሉት ተቋማት ያመነጫቸዉ የሙስና ወንጀል መረጃ ጥቆማዎችን ዳሰሳ ያደረገ፤
   3. በዘርፉና በሥሩ ባሉት ተቋማት የመልካም አስተዳደር እና የተገልጋይ እርካታ ችግሮችን በተደጋጋሚ በሚታይባቸዉ አሰራር ሥርዓት ከባቢን ትኩረት ያደረገ፤
   4. የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ እንዲሁም ትክክለኛነት የማረጋገጥ ሥራ አፈጻጸም ዝቅተኛ ደረጃ የሆነ ዘርፍና ተቋም፤
   5. ከፍተኛ ሀብት የሚያስተዳደር እና ፕሮጀክቶችን የሚያከናዉን ዘርፍ/ተቋም፤
   6. ዘርፍ-ተኮር የፀረ-ሙስና ትግል ተግባራትን ለመፈጸም ቁርጠኝነት የማይታይበት ዘርፍ/ተቋም፤
   7. በተመጣጣኝ እና ወጪ ቆጣቢ ሆኖ መከናወን የሚችል፤
   8. የፕሮፖዛል ዝግጅት ጊዜን ጨምሮ በ75 የሥራ ቀናት ውስጥ የተሟላ ጥናትን ለማካሄድ ብቁ የሆነ፤
   9. በበጀት ዓመቱ ነሐሴ ወር ውስጥ የጥናት ፕሮጀክት ፕሮፖዛል ተጠናቆ የፀደቀ፤
   10. የጥናት ተግባራትን ማከናወን የሚችሉ የኮሚሽኑንና ከየተቋማት የየተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍል የተካተቱበት ብቁ የጥናት ባለሙያዎችን ቡድን የያዘ፤

11. የጥናት ሥራ ለማከናወን እና ለሚመለከተዉ ዘርፍ/ተቋም ምክረ-ሐሳብ ለማቅረብ ግልጽ የድርጊት መርሃ-ግብር ያለዉ፤

12. የጥናት ፕሮጀክት ፕሮፖዛል እና ድርጊት መርሃ-ግብር አጠቃላይ እስከ 15 ገጽ ሆኖ የተዘጋጀ፤

13. በሥራ ክፍሉና በዘርፉ ግምገማ 75% እና ከዚያ በላይ የፕሮፖዛል ዝግጅት ጥራትና ተገቢነት ያገኘ እና በማኔጅመንት ኮሚቴ ግምገማ ቢያንስ 75% ያላነሰ ያገኘ እና ከላይ ከተዘረዘሩት ዋና ዋና መስፈርቶች ውስጥ የተወሰኑትን የሚያሟላ የሙስና መከላከል ጥናት ፕሮጀክት ፕሮፖዛል ተቀባይነት ያገኛል፡፡

## 6. የሙስና መከላከል ጥናት ዋና ዋና አሰራር ሂደት፤

1. በማኔጅመንት ኮሚቴ ፀድቆ በጀት የተመደበለት የጥናት ፕሮጀክት ፕሮፖዛል ያለው መሆኑ፤
2. በታቀደዉ መሰረት፤ በቂና ተገቢነት ያለው መረጃና ማስረጃ ማመንጨት መቻል፤
3. በፕሮፖዛሉ የተመላከተዉን ቁልፍ የዘርፉን/ተቋሙን ችግር ለመፍታት አግባብት ያለዉን ምክረ-ሐሳብ ማመንጨት የቻለ፤
4. የተሰበሰበዉን መረጃና ማስረጃ በማደራጀት፤ በመተንተን እና ረቂቅ ሪፖርት በማዘጋጀት በዘርፉ ግምገማ ተደርጎ ተቀባይነት ያገኘ፤
5. የጥናት ፕሮፖዛልን ጨምሮ አጠቃላይ የጥናት ሥራዎችና ሪፖርት ዝግጅት ከ75 የስራ ቀናት በላይ ያልወሰደ፤
6. የጥናቱ ዓላማ የሆነዉን ዋናዉን ዘርፉን/የተቋሙን የሙስና ሥጋትና ተጋላጭነት ችግር ለመፍታት ማስረጃ-መር ምክረ-ሐሳብ ማመንጨት የቻለ፤
7. በማኔጅመንት ኮሚቴ የጥናቱ ጭምቅ ኃሳብ እስከ ሶስት ገጽ እና ዋናዉን ሪፖርት እስከ 25 ገጽ ቀርቦ ተገምግሞ የፀደቀ እና ለሚመለከተዉ ዘርፍ/ተቋም ምክረ-ሐሳብ እንዲቀርብ የተወሰነ መሆን ይኖርበታል፡፡

## 7. የሙስና መከላከል የአሰራር ስርዓት ጥናት የሪፖርት ይዘት

1. እስከ ሶስት ገፅ የጥናቱ ጭምቅ ኃሳብን የያዘ፣
2. መግቢያ፣
3. የጥናቱ ዋና ዓላማና ግብ፣
4. የጥናቱ መረጃ ምንጮችና የተገኙ መረጃዎችና ማስረጃዎች፣

5. የጥናቱ ዋና ዋና ግኝቶች በየርዕሰ ጉዳይ፣
6. ከጥናቱ ግኝት ጋር ተናባቢ የሆነ የጥናቱ ምክረ-ሐሳብ፣
7. የጥናቱ ምክረ-ሐሳብ የድጋፍ እና የክትትል ስልት፣
8. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች፣
9. ማጠቃለያ
10. አጠቃላይ የጥናት ሪፖርት ገፅ ብዛት ከ25 ገፅ ያልበለጠ፣
11. ዋቢ ማጣቀሻዎችን ያካተተ መሆን አለበት፡፡

## 8. የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች በሙስና መከላከል ጥናት ስለሚኖራቸው ተሳትፎ፣

የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች በሙስና መከላከል ጥናት ባለሙያዎች ስራ ላይ የሚከተለው ተሳትፎ ይኖራቸዋል፡-

1. ኮሚሽኑ በሚያጠናው የሙስና መከላከል ጥናት ውስጥ እንዲሳተፉ ይደረጋል፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የስነምግባር መከታተያ ክፍሎች በዘርፉ ውስጥ በሚታዩ፡-
   ሀ/ በግዥና ውል አስተዳደር፣
   ለ/ በንብረት አስተዳደርና አጠቃቀም፣
   ሐ/ በፕሮጀክት ትግበራና ክትትል፣
   መ/ ከፍተኛ የሙስና ስጋት ያለባቸው የስራ ክፍሎች ጋር የተያያዙ ጉዳዮች፣
   ሠ/ በአመራሮችና ሰራተኞች ሥነምግባር እና በዉሳኔ አሰጣጥ የጥቅም ግጭት ተጋላጭነት ዙሪያ ጥናት የሚያጠኑ ይሆናል፡፡
3. የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ 2 የተመለከቱትን ጥናቶች ለማጥናት በዘርፍ ደረጃ የተዘጋጀውን የጥናት ፕሮፖዛል ለኮሚሽኑ በማቅረብ ማፀደቅ ይኖርባቸዋል፡፡

## 9. የሙስና መከላከል ጥናት ስራ ክንውን ጊዜ

1. የሙስና መከላከል ጥናት ስራ የጥናት ፕሮጀክት ፕሮፖዛሉን ጨምሮ በ 75 የስራ ቀናት መጠናቀቅ ይኖርበታል፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው ቢኖርም የጥናት ስራው ውስብስብ ባህርይ ያለው ከሆነ፣ ከአዲስ አበባ ውጭ ከአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ክልሎች

መንቀሳቀስን የሚጠይቅ ከሆነ እና ጥናቱን በተቀመጠው ጊዜ ማጠናቀቅ አለመቻሉን ተጨባጭ የሆነ ምክንያት መኖሩ ከተረጋገጠ በኮሚሽኑ የበላይ አመራር እየታየ የጊዜ ገደቡ ሊጨመር ይችላል፡፡

## ክፍል ሶስት
## የሙስና መከላከል ጥናት ፕሮጀክት የትግበራ ምዕራፍ ሥራዎች

### 10. የጥናት ሪፖርት ዝግጅትና ግምገማ ሥራዎች፤

1. የጥናት ሪፖርቱ እስከ 25 ገጽ እና ጭምቅ ኃሳብ እስከ 3 ገጽ የያዘ ለኮሚሽኑ የመረጃ ማዕከል ማስረከብ፤
2. ለጥናት ፕሮጀክቱ የተሰበሰቡ ማስረጃዎችና መረጃዎችን ለብክነት እንዳይጋለጥ በማደራጀት፤ ለኮሚሽኑ የመረጃ ማዕከል ማስረከብ፤
3. የጥናት ሪፖርቱንና ምክረ-ሐሳቡን መነሻ በማድረግ፤ ከዘርፉ/ተቋሙ ሥነምግባር መከታተያ ክፍል ጋር የምክረ-ሐሳብ ድርጊት መርሃ-ግብር ማዘጋጀት እና ማከናወን፤
4. የተጠኑ ጥናቶች ምክረ-ሐሳብ ትግበራ ውጤታማነት ጥናቱ በተጠናበት በጀት ዓመት ውስጥ የድጋፍ፤ ክትትልና ግምገማ ሥራዎችን በየወቅቱ ማከናወንና ሪፖርት ለማኔጅመንት ኮሚቴ ማቅረብ፤
5. በተጠኑ ጥናቶች ላይ የሚደረግ የድጋፍና የክትትል ስራዎች አተገባበር ከተቋሙ የበላይ አመራር ጋር ስምምነት ላይ በመድረስ በማድረግ ማከናወን፤
6. የተጠኑ ጥናቶች በቀረበው ምክረ ኃሳብ መሰረት መተግበራቸውን በመረጃና ማስረጃ ላይ ተመስርቶ ማከናወን፤
7. በተጠናው ጥናት መሰረት የቀረበውን የጥናት ምክረ ኃሳብ ማሻሻያ ተግባራዊ በማያደርጉ አካላት ላይ በኮሚሽኑ ማቋቋሚያ አዋጅ መሠረት በሕግ የመመርመርና የመክሰስ ስልጣና ላለው አካል እንዲተላለፉ ይደረጋል፡፡
8. የጥናት ሪፖርቱን ለስልጠና እና ግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ማዋል፤

## 11. የጥናት ባለሙያዎች ቡድን የሥነምግባር ሁኔታዎች፤

1. ለጥናት ዓላማ የተገኘዉን መረጃና ማስረጃ ምስጢራዊነቱን መጠበቅ፣
2. ለሥራዉ የሚያስፈልገዉን ዕዉቀት፤ ክህሎት እና የሥራ ቦታ ሥነምግባር መተግበር፤
3. ከዘርፍ/ተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች (የጥናት ባለሙያዎች) ጋር በቅንጅትና በትብብር የመሥራት ባህል ማዳበር፤
4. ነጻና ገለልተኛ አቋም በመያዝ የጥናት ዉጤትን ከጥቅም ግጭት ነጻ ሆኖ ማዘጋጀት፤
5. የዘርፍ/የተቋም የአሰራር ሥርዓት ግልጽነት እና ተጠያቂነት ባህል ለመገንባት ገንቢ ሚና መጫወት፤
6. ያልጸደቀ የጥናት ፕሮጀክት ተግባራዊ አለማድረግ፤
7. ያልጸደቀ የጥናት ሪፖርት ለማንኛዉም አካል ይፋ አለማድረግ፤
8. የጥናት ሥራዉን በቡድን ማካሄድና የቡድኑን የጋራ ዉሳኔ ማክበር፤
9. የጥናት ፕሮጀክት ተግባራትን በተሰጠዉ የጊዜ እና በጀት ገደብ ዉስጥ ለማጠናቀቅ ትኩረት ማድረግ፤
10. በጥናት ሂደት ለዕዉነት እና ለዕዉቀት ቅድሚያ የመስጠት፣
11. ጥናቱ ወቅት የተፈፀመ የሙስና ወንጀልን የሚያሳይ መረጃና ማስረጃ ከተገኘ ይህንኑ ለሙስና መከላከል ዘርፍ በማሳወቅ ለዲጂታል ሙስና መረጃ አስተዳደር እንዲተላለፍ መደረግ አለበት፡፡

## 12. የበጀቱ ዓመቱ የጥናት ስራ መጀመሪያ ጊዜ

1. በበጀት ዓመቱ የሚከናወን የሙስና መከላከል ጥናት ስራ የሚጀመረው በየዓመቱ ነሐሴ 1 ቀን ይሆናል፡፡
2. የበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ወር የተጠኑ ጥናቶች ክትትልና ድጋፍ ለማድረግና አገር አቀፍ የሙስና መከላከል ጥናት ጉባኤ የሚካሄድበት ጊዜ ይሆናል፡፡

The Federal Ethics and Anti-Corruption Commission

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

13. **ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው አሰራሮች**

ከዚህ ፕሮቶኮል ጋር የሚቃረኑ ማናቸውም ልማዳዊ አሰራሮች በዚህ ፕሮቶኮል በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

14. **ፕሮቶኮሉን ስለማሻሻል**

ይህን ፕሮቶኮል ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በኮሚሽኑ ሊሻሻል ይችላል::

15. **ፕሮቶኮሉ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ፕሮቶኮል ከፀደቀበት ከሐምሌ 4 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ፤ ሐምሌ 4 ቀን 2017 ዓ.ም

ሳሙኤል ኡርቃቶ (ፒኤች ዲ)

የፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን

ኮሚሽነር